በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር Ref. No. 1.0/831
ቀን Date 16 ሰኔ 2006

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያቁጥር 46/2002 ን ለማሻሻል የወጣውን መመሪያ ቁጥር 99/2006 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

በከር ሹሉ ዱሊ
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይን ልማት ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለቅርንጫ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለህግ ጥናትና ረቂቅ ዝግጅት ቡድን
- ለጉምሩክ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ሰኔ 2006

# የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

በዕቃዎች የዓለም አቀፍ ዝውውር በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የመጠን ወይም የክብደት ልዩነቶች መኖራቸውን በመገንዘብና በተለይ በዚሁ እረገድ ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ቅሬታዎችን መፍትሄ ለመስጠት አግባብነት ያለው የመጠን ወይም የክብደት ልዩነት ማርጅን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112 መሠረት ይህንን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር99/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

በመመሪያው አንቀጽ 4 ስር የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤

(3) የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ በሚፈጠር የክብደት ልዩነት ምክንያት በቀረጥና ታክስ ላይ የሚኖረው ልዩነት ቀደም ሲል ከተከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን ከ5% የማይበልጥ ከሆነ የልዩነቱን ቀረጥና ታክስ ብቻ ያለቅጣት በማስከፈል በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛል፡፡

3. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ተመሳሳይ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

4. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በከር ሻሌ

የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

# የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ሰኔ 2006

## የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

በዕቃዎች የዓለም አቀፍ ዝውውር በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የመጠን ወይም የክብደት ልዩነቶች መኖራቸውን በመገንዘብና በተለይ በዚሁ አረገድ ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ቅሬታዎችን መፍትሄ ለመስጠት አግባብነት ያለው የመጠን ወይም የክብደት ልዩነት ማርጅን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112 መሠረት ይህንን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር99/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

   በመመሪያው አንቀጽ 4 ስር የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤

   (3) የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ በሚፈጠር የክብደት ልዩነት ምክንያት በቀረጥና ታክስ ላይ የሚኖረው ልዩነት ቀደም ሲል ከተከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን ከ5% የማይበልጥ ከሆነ የልዩነቱን ቀረጥና ታክስ ብቻ ያለቅጣት በማስከፈል በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛል፡፡

3. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

   ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ተመሳሳይ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

4. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

   ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በከር ሻሊ

የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

# የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ሰኔ 2006

## የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 99/2006

በዕቃዎች የዓለም አቀፍ ዝውውር በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የመጠን ወይም የክብደት ልዩነቶች መኖራቸውን በመገንዘብና በተለይ በዚሁ እረገድ ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ቅሬታዎችን መፍትሄ ለመስጠት አግባብነት ያለው የመጠን ወይም የክብደት ልዩነት ማርጅን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112 መሠረት ይህንን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር99/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   በመመሪያው አንቀጽ 4 ስር የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤

   (3) የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ በሚፈጠር የክብደት ልዩነት ምክንያት በቀረጥና ታክስ ላይ የሚኖረው ልዩነት ቀደም ሲል ከተከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን ከ5% የማይበልጥ ከሆነ የልዩነቱን ቀረጥና ታክስ ብቻ ያለቅጣት በማስከፈል በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛል፡፡

3. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

   ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ተመሳሳይ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

4. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በከር ሻሌ

የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር